
ኢትዮ - ትረካ
ከንኪን ዳና ሞዐጡ ! !
@ethio_terka
TAFT
PHOTOGRAPHY

‹‹ልክ ነህ›› አለ ደስታ እራስ ምታቱን ስላስታወሰበት ትንሽ ቅር እያለው::

"ምነው አስቀየምኩ እንዴ ዶ/ር" አለ እስረኛው::

"ኧረ በፍጹም"መለሰ ደስታ::

"ታዲያ ምነው ዝም ብለህ ቀረኽ" ሲል ጠየቀው::

"እይ የምትላቸውን ነገሮች አስቤ እየተገረምኩ ነው" አለ ደስታ::

"ለምን?"

" የሚሰማ መጥፉቱ ነው እንጂ ሁላችንም የምንናገረው ስንት ቁም ነገር ነበር ብዬ" አለው:: እስረኛው ራሱን በመነቅነቅ መስማማቱን ገለጸለት::

Scanned by CamScanner

ሦስት በድምቀት

ደስታ ሌሊቱን ሙሉ በከባድ ራስ ምታት ሲሰቃይ አድሮ ጠዋት ከብዙ ጭቅጭቅና ንትርክ በኋላ የእስር ቤቱ ሃኪም ጋር እንዲቀርብ ተፈቀደለት::

የእስር ቤቱ ክሊኒክ ከግቢው አንድ ጥግ ላይ ቦታ እንደምንም ተፈልጎለት ሻጥ የተደረገ የሚመስል ክፍል ነው:: እስረኛውን ለመቅጣት ተብሎ ይሆን የሚል ሃሜትን በቀላሉ ሊፈጥር የሚችል ነው::

ደስታ ህመሙ ስለበረታበት በመጠኑም ቢሆን ተጨንቋል:: የህክምና ቤቱን ሲያይ ግን ከህመሙ በላይ ጭንቀቱ በረታበት:: እዚህች ክፍል ውስጥ ሊያገኝ የሚችለውን ባለሙያ ማመን እንደማይችል ያውቃል::

ህክምና እምነት ነው ብሎ የሚያምነው ደስታ፣ እንዲህ ካለ ቤት ውስጥ ምንም ዓይነት ሊታመን የሚችል ህክምና ይገኛል ብሎ ለማሰብ አልቻለም:: የቤቱ መድከም ለእስረኞቹ ህክምና ብቻ ሳይሆን፣ ሰባስሞያዎቹም የተሰጠው ትኩረት ምንኛ የወረደ መሆኑን አመልካች ነው:: በርግጥ የሚያምር ህንጻም ቢሆን መልካም ህክምና ይገኝበታል ማለት አይደለም:: ቢሆንም ግን እንዲህ በመፍረስ ላይ እያለ ሃሳቡን

Scanned by CamScanner

የቀየረ የሚመስል ቤት ውስጥ ትርጉም ያለው ህክምና ማግኘትን፣ መመኘት የዋህነት ብቻ ሳይሆን አላዋቂነትም ነው።

ደስታ ይህን እያወቀም ቢሆን እንኳን በዚህ ክፍል ውስጥ መታየት ግዴታው መሆኑን አምኗል። መኖር የሚቻለው በጊዜው እና በቦታው ለመኖር በተዘጋጀው ብቻ ነው ብሎ ስለሚያምን። ወደ ክፍሉ ውስጥ ሲዘልቅ የህክምና ልብሱና የፊቱ ቆዳ ከቤቱ ግድግዳ እኩል የበለዙበት ባለሞያ ተቀምጦ አየ።

"ምን ነበር አለ ባለሙያው ለሰላምታና ለመሳሰሉት የታካሚ ጭንቀት ማለዘቢያ ዘዴዎች ጊዜም ፍላጎትም እንደሌለው በሚያስታወቅ እይታ። ደስታ ባለሙያው በአንድ ወገን ከዚህ ውስጥ እየሰራ በመዋሉ በማዘንና ምናልባትም በቂና ተገቢ ስልጠና ያላገኘ ባለሙያ ሊሆን ይችላል በሚል ግምት፤ በሌላ ወገን ደግሞ የራሱም የሙያ ግዴታ መስሎ ስለተሰማው አጋጣሚውን ተጠቅሞ እውቀቱን ለማካፈል በማሰብ፤

" አንድ ሰው እኮ ታሞ ባለሙያ ጋር ሲቀርብ ቢያንስ ሦስት ነገሮች ያስፈሩታል" አለ። ባለሙያው ካቀረቀረበት አንካሳ ጠረጴዛ ቀና ብሎ ደስታን ከየት የመጣ ነው በሚል ዐይን አየው። ምናልባትም ደስታ መንገድ ተሳስቶ የመጣ ሳይመስለው አልቀረም።

ደስታ ባለሙያው ምንም ንግግሩን እንዲቀጥል የሚያበረታታ ዓይነት ግብዣ ባያሣየውም የራሴን ሃላፊነት መወጣት አለብኝ በሚል ሞራል ንግግሩን ቀጠለ

"እንደኛ፣ ምን ይሆን ያመመኝ ብሎ ይፈራል ። ሁለተኛ፣ የህክምና ባለሙያው እንዴት ያስተናግደኝ ይሆን ብሎ ይሰጋል። ሦስተኛ፣ ከህመሜ እንዴት እፈወስ ይሆን ብሎ ይፈራል ብሎ አጭር ትምህርቱን ደመደመ።

" ምን ነበር? አለ ሞያተኛው። ደስታ መጀመሪያ የተጠየቀውን ጥያቄ ያልሰማ ስለመሰለው።

Scanned by CamScanner

"ራሴን አሞኝ ነበር የመጣሁት" አለ ደስታ። አነጋገሩንም ምኞቱንም አሳምሮ።

እሺ። ይህንን መድሃኒት ሲያምህ ሲያምህ ሁለት ሁለት ፍሬ ዋጥበት" ብሎ መድሃኒት ከመሳቢያው በማውጣት ለደስታ ካቀበለው ቦኋላ እስክሪቢቶውን ወደ ደስታ በማዞር

እዚህ ጋር ፊርማ ፊርም አለው። ከደስታ ስም ትይዩ የፊርማ ቦታ እያሳየው። ደስታ የክብር ፊርማውን በመሸማቀቅ አስቀምጠ ከመቀመጫውበመነሳት"አመሰግናለሁ ብሎ ወጣ።

"ምንም አይደልም አለ ባለሙያው። ሁለቱም የለመዱትን ቃላት እየወረወሩ መሆኑን አላስተዋሉም ነበር።

ደስታ ከህክምናው መልስ ምንም እንኳን ራስ ምታቱ በህመም ማስታገሻ የማይስተካከል እንደሆነ ቢገባውም ለማንኛውም በማለት ሁለት ፍሬ ውጦ ምን ማድረግ እንዳለበት ማሰብ ጀመረ።

አሁን ፊርቷል። በዚህ ዓይነት ህክምና ያመመው ነገር ቀላል ቢሆንም እንኳን እየቆየ ሊከፋ እንደሚችል ስለተገነዘበ። በህክምናው ሁኔታ መናደድ ምንም ፋይዳ እንደማይሆንለት ያውቃል። እንዴት አድርጎ የተሻለ ህክምና ሊያገኝ እንደሚችል በማሰብ ላይ እንዳለ

"ታራሚ ደስታ ጠየቂ መጥቷል" የሚል ድምጽ እንደተለመደው ቀሰቀሰው።

"እሺ" ብሎ ወደ መጠየቂያው አመራ።

ውቢትና ሰብለ ከአግዳሚው ማዶ ሆነው የደስታን ፊት ሲያዩ በጣም ተደናገጡ።

"ምነው፣ ደህና አይደለህም አለች ሰብለ። ለሰላምታም ጊዜ ሳትሰጥ።

"ራሴን አሞኝ ነው አለ።

Scanned by CamScanner

"ይህን ራስ ምታት ግን በቃ ዝም ብለህ ታያለህ አለች ሆዷ መግፋት የጀመረው ውቢት በወቀሳ። ከዚህ ቀደም ደጋግማ እንዲመረመር ስትወተውት ስለነበር ትንሽ ንዴት ቢጤም እየተሰማት።

"ሄጄ ነበር አለ ደስታ።

"እና ምን ተባልክ?" ሰብለ ነበረች።

"የህመም ማስታገሻ ሰጡኝ" አለ ደስታ ስለ ህክምናው ሁኔታ በመንገር ያልተፈለገ የመብት ክርክር ውስጥ ሰብለ እንድትገባ አልፈለገም።

"እና ተሻለህ?" አለች ሰብለ ትኩረቷ አሁንም የፊቱ መጥቆር ላይ ነበር።

" ምንድን ነው ተባልክ? " አለች ውቢት። ደስታ ለውቢት ጥያቄ አልተዘጋጀም። ምክንያቱም የፈራውን የህክምና ሁኔታ ማስረዳት ግድ እንዳይለው ስለሰጋ።

"ሰላም ነው" አለ።

"ሰላም ነው የሚባል በሽታ አለ? " አለች ውቢት ኮስተር ብላ።

"አይ ብዙም ችግር የለውም" አለ።

ሰብለ በደስታና በውቢት መካከል ግልጽ ያልወጣ ክርክር መኖሩን የጠበቃነት ስሜቷ ነገራት። "ምን ችግር አለ እኔ የማላውቀው?"አለች

"ምንም የለም " ኣሏት ሁለቱም በአንድ ቃል።

"ተዉ እንጂ! እናንተ ብቻ ሃኪሞች አይደል! ሁሉንም በምስጢር የምትነጋገሩት" አለች በማሽሟጠጥ።

ደስታ ነገሩ ሳይከር ለማብረድ በመሞከር

"አይ ብዙ ችግር የለውም። ለማንኛውም ጥሩ ሃኪም ያለበት ቦታ እንልክሃለን ብለውኛል" ብሎ ዋሸ።

Scanned by CamScanner

ውቢት በደስታ ንግግር ግራ በመጋባት "አንተ ጥሩ ሃኪም የት እንዳለ ጠፍቶህ ነው እነሱ የሚልኩህ?" አለችው።

ለብለ የሁለቱም ንግግር ስላልጣማት "ችግር የለም። እኔ ገብቼ አነጋግራቸዋለሁ። መታየት ያለብህ ቦታ ትታያለህ" አለች።

"እስኪ ለማንኛውም ጥቂት ቀን ልየው፣ ይሻለኛል" አለ ደስታ።

"ደስትሽ መቼም ይኼን ላንተ አላስረዳህም ዩ....." ብላ ውቢት ንግግሯን በአጭሩ ቀጨችው።

Scanned by CamScanner

ሠላሳ ስድስት

ደስታ ከሰብለና ውቢት ጉብኝት በኋላ በምን መልክ የተሻለ ህክምና ሊያገኝ እንደሚችል ማሰላሰል ጀመረ። በህይወቱ በየትኛውም ጊዜ እሱ ህክምና አስፈልጎት የሚያጣ መስሎት አያውቅም ነበር። አሁን ነገሩ ሁሉ በጣም ገረመው።

ደስታ በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን አክሟል፤ እንዲታከሙ ረድቷል። ለብዙዎች የሚያክሟቸውን ሰዎች አስተምሯል፤በእጁ ብዙ ሰው ተፈውሷል፤ ብዙዎችም አልፈዋል። በሃኪምነቱ ራሱን የሰው ልጅ መከራ ታዛቢ አድርጎ ከማየት በዘለለ የመታበይ ስሜት ለደቂቃም ኖሮት አያውቅም።

የህክምና አገልግሎት ችግር በብዛት እንዳለ ቢያውቅም እሱ ራሱ አገልግሎት ሊያጣ እንደሚችል ግን አስቦ አያውቅም። እስር ቤት ውስጥ ህክምና እንደሚሰ፡ጥ የሩቅ እውቀት ነበረው። ከዚያ ውጪ ግን ህክምናው ምን ይጨምር ምን ይቀንስ አያውቅም ነበር።

አንዳንድ ጊዜ እውነት እንደድንጋይ ሲማታ ያማል። በአንድ ቦታ በራስ ዙሪያና አካባቢ ብቻ ተወስነው ሲኖሩ ሌላ ዓለም መኖሩን መዘንጋትን ያስከትላል። ደስታ ከእስር ቤት እጃቸውን ታስረው ወደ እሱ የሚሰራበት ሆስፒታል የሚመጡ እስረኞችን በተደጋጋሚ በግቢው ውስጥ እንዳላየ አልፏቸዋል። አሁን ምናልባት እሱም እጁን ታስሮ ከሌላ እስረኛ ጋር በመጣመር በተሰላቹ ጠባቂዎች እየተገፈተረ በክብር

Scanned by CamScanner

ይሰራበት ወደነበረው ሃኪም ቤት በእስር መሄድ ግድ ሊሆንበት ይችላል::

አንዳንድ ጊዜ ህይወትን ከስርም ከላይም ማየት ግርምትን የሚፈጥር ትዕይንት ነው:: 'ማንነት' በትልቁ ተወጥሮ የተነፋ ፊኛ እንደማለት ነው በትንሽ እሾህ ሲበሳ ተንፍሶ ኢመንት የሚሆን:: ሰው ኢመንት ነው፤ሰው ተራ ነው፤ሰው አቅም የለውም፤ሰው ደካማ ነው:: ይህም ሆኖ ግን አብዛኛውን ጊዜያችንን የምናጠፋው ይህንኑ ኢመንትነት ለመርሳት በመጣር ነው::

የሰው ልጅ ሲወለድ ከእሱ ብቸኝነት በመቀጠል የሚረዳው ጉዳይ ደካማነቱን ነው:: ለመብላት፣ለመጠጣት፣ንፁህ ለመሆን፣ ለመሞቅ፣ ለመቀዝቀዝ ሌሎች የግድ አስፈላጊ መሆናቸው አይቀሬ ነው:: ደስታ አሁን ሰው እንደሚያስፈልገው ከመቼውም በላይ አምኗል:: ሃያ አራት ሰአት ሙሉ በራስ ምታት መደ:ብደቡ ሰልችቶታል:: ምንም እንኳን ለራሱ ጥቅም ሲል የግል ደረጃውንና ግንኙነቶቹን መጠቀምን እንደጥፋት ቢቆጥረውም ሰብለንና ወንድሙን ተጠቅሞ ወደ ሆስፒታል የሚሄድበትን መንገድ ማመቻቸት እንዳለበት ወስኗል:: ይህንንም ከማድረጉ በፊት አንድ ዕድልን ለመሞከር በማሰብ ወደ ጠባቂው ፖሊስ ሄደ::

"ህመሜ በጣም ስለባሰብኝ ወደ ሃኪም ቤት መሄድ የግድ ያስፈልገኛል" ሲል በአፅንዖት አመለከተ::

ፖሊሱ "ነገ ጠዋት ወደ እስር ቤቱ ሃኪም ቤት እንወስድሃለን እዚያ ዶ/ር ስላለ እሱ ያይሃል" አለው:: ምንም ማብራሪያና ማሳመኛ ሳይፈልግ ::

ደስታ የጠበቀውን ምላሽ ከፖሊሱ ባለማግኘቱ በመገረም "እሺ አመሰግናለሁ እግዜር ይስጥልኝ" አለ:: ፖሊሱ እንደባለፈው ጊዜ ችግሩን አቅልሎ ያይብኛል ብሎ በመፍራት ነበር ደስታ ጥያቄውን ያቀረበው፤ ሆኖም ምላሹ በተገላቢጦሽ መልካምና አዎንታዊ ሆኖ

Scanned by CamScanner

ስላገኘው ፖሊሱ በምን መመዘኛ እንደሚወስን ለመረዳት ባለመቻሉ እየተገረመ እስኪነጋ ድረስ ሰዓቱን መቁጠር ጀመረ።

አቤት በህመም ጊዜ ሰዓት እንዴት ይረዝማል! ህመምና መከራ ጊዜን የማቆም ምትሃታዊ ሃይል ሳይኖራቸው አይቀርም። ደስታ ጊዜውን በመተኛት፣ በመነሳት፣ በማሰብ፣ መፅሐፍ በማንበብ ከሌሎች እስረኞች ጋር መዝመር በመዘመርና ዐይኑን ጨፍኖ እስከ መቶ በመቁጠር ለማሳለፍ ቢሞክርም ነገ አልመጣም አለው። አሁን ህመምና የመታከም ጉጉት አቅም ነሱት እንጂ፤ ደስታ ከማንም ሰው በላይ 'ነገ' የሚባል ቀን የለም ብሎ ይከራከር የነበረ ነው።

'ህመም' አንዱ የመኖርን ጊዜያዊነት አስታዋሽ ስለሆነ፤ ደስታንም እንኳን ከእምነቱ ነቀነቀው። የአለመኖር ፍርሃት ሰውን ባመነበት እንዳይፀና፤ ባመነበት እንዳይቆም፤ የሚለውን እንዲከዳ፤ያልሰራውን እንዲበላና የሌላውን እንዲቀማ ይገፋዋል።

ደስታ ሌሊቱ ነግቶ በጠዋት ወደ የተባለው የእስር ቤት ሆስፒታል ሲወሰድ ህልም ህልም መሰለው።

የእስር ቤቱ ሃኪም ቤት በብሎኬት የተገነባ ሆኖ መደዳውን ለመኝታ ቤት የሚያገለግሉ አዳራሽ መሳይ ህንፃዎች አሉት። በአንዱ አዳራሽ ውስጥ ወደ ሰላሳ የሚጠጉ አልጋዎች ተቃቅፈው ተደርድረዋል።

ሃኪሙ ደስታን ከመረመረው በኋላ የራስ ምታቱን መፍትሄ ለማወቅ እንዲረዳው በማሰብ ሃኪም ቤት እንደሚያስተኛው የነገረው በትዕዛዝ መልክ ነበር። ደስታ እዚህኛውም ሃኪም ጋር የልቡን የማውራት ዕድል ባለማግኘቱ ቢያዝንም፣እዚያች እስር ቤት ውስጥ ቁጭ ብሎ ራስ ምታቱን ከመቁጠር ሃኪም ቤት ውስጥ ቢተኛ የተሻለ ይሆናል ብሎ በማሰብ ለመተኛት ተስማማ።

Scanned by CamScanner

ሠላሳ ሰምንት

በመኝታ ክፍሉ ውስጥ ሁሉም ዓይነት ህመምተኛ አለ። ደስታ ከህመምተኞች መካከል በመኖር ዕድሜውን ቢያሳልፍም፤ ከህመምተኞች ጋር መተኛትን በቀላሉ ሊለምደው አልቻለም። የመጀመሪያ ችግሩ የሌሎችን ህመም እየሰማ ራሱን በማስተዛዘን ብቻ መወሰኑ ከበደው። ከዚያ በመቀጠል ህመምተኞቹ ሀኪሙን፣ ሌሎቹን ባለሞያዎችና ህክምናውን ሲያሙ አብሮ ማማት ሊዋጥለት አልቻለም። ሀኪምነቱ ከታካሚነቱ ጋር ተደበላለቁበት።

ከዚህም በላይ ግን ያስቸገረው ጠያቂ እንደፈለገው አለማግኘቱ ነበር። ሰብለን በየቀኑ ሊያያት አልቻለም። ከብቸኝነት ጋር ክፉኛ ተፋጧል።

ይህንንም ሁሉ ችሎ፤ የራስ ምታቱ እየበረታበት በመሄዱ አብዛኛውን ጊዜ በአልጋ ላይ ተኝቶ ነው የሚያሳልፈው። ከዕለት ወደ ዕለት የግራ አግሮቹና እጆቹ እየደከሙበት ስለመጡ፤ እዚያው አልጋ ላይ እንደተኛ እጥፍ ዘርጋ በማድረግ ሊያበረታቸው ይጥራል።

ሃኪሙ የተቻለውንና የሚችለውን አድርጓል፤ እያደረገም ነው። የደም ምርመራዎችን አሟል፤ ሽንት መርምሯል። ከዚህ የተለየ ምርመራ በዚህ ሆስፒታል ሊያደርግ አይችልም።

ሰብለ በራሷ መንገድ ሄዳ ወደ ሃኪም ቤቱ ተመላልሳ የምትጠይቅበትን ፈቃድ ለማግኘት አምስት ቀናትን ያህል ፈጅቶባት ደስታን

Scanned by CamScanner

ልትጠይቀው መጥታለች። ደስታን ከአልጋው ጋር ተጣብቆ ስታየው ህመሙ ከሚለው በላይ እንደባሰበት ለመገመት ብዙም ጊዜ አልፈጀባትም።

ደስታ አልጋው ላይ እንደተንጋለለ ሰብለን ሲያያት ደስ አለው። ከአልጋው በስተግራ ተጠግታ ከንፈሮቹን ሳመችው። ደስታ አፀፋውን በመመለስ ናፍቆቱን ገለፀላት።

"እንደምን ነሽ ስላየሁሽ በጣም ደስ አለኝ" አለ በዝግታ። ድምፁ እንደወትሮው ልበ ሙሉነት አይስተዋልበትም። ሰብለ ሆዷ ተረበሸባት።

"ደስትሽ ደህና አይደለህም? ባሰብህ? ምን ላድርግልህ?" አለች ስትናገር ከንፈሮቿ እየተሳሰሩባት ነበር። ደስታ የሰብለን መረበሽ ቢያይም ሊያባብላት አቅም አልነበረውም። ከዚህ ቦታ መውጣት እንዳለበት አምኗል። እዚሁ ከቆየ ህመሙ ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት አልቻለም። አንድ ርግጠኛ የሆነበት ጉዳይ ቢኖር ያመመው ህመም ተራ ራስ ምታት አለመሆኑን ብቻ ነው።

"ክብሩን ደውለሽለት አንድ ቦታ ህክምና እንዳገኝ ቢረዳኝ" አለ ደስታ በልመና። ሰብለ እንባዋን ማቆም አልቻለችም ።

"በቃ ባሰብህ ማለት ነው?" አለች፤ ደስታን ምንም እየረዳችው እንዳልሆነ ብታውቅም ዝም ብላ ማየት ስላልቻለች።

"ደህና እሆናለሁ! ከአደጋው ጋር የተያያዘ ይመስለኛል" አለ ደስታ።

"ከአደጋው ጋር ምን?" ስትል ጠየቀች ሰብለ የታመመ ሰው ከሚጠላው ነገር አንዱ የገዛ ህመሙን ማብራራት መሆኑን ባለማስተዋል።

"ለማንኛውም ክብሩን ደውይለት፤ መኮንንም ሊረዳኝ ይችላል" አለ ደስታ። በህይወቱ ቅርብ የሆኑ ሁለት ሰዎችን ጓደኛውን እና ወንድሙን በጣም አርቆ እርዳታቸውን መጠየቁ ለሰብለ ግራ ቢገባትም ለምን ብላ አልጠየቀችውም።

Scanned by CamScanner

"እሺ" ብላ ስልኳን ለማውጣት ስትሞክር፤ ወደ እስር ቤቱ ስትገባ በር ላይ አስቀምጣው ስለመጣች ስልኳን አላገኘችውም።

"በቃ ሂጂ እና ደውይላቸው" አላት ደስታ።

"እሺ" ብላው ከአልጋው መራመድ እንደጀመረች ወደኋላ መለስ ብላ አየችው።

"ምነው?" አላት ደስታ ቢደክመውም ከፊቷ ልትነግረው የፈለገችው ጉዳይ እንዳለ ለማንበብ ችሏል።

"ግድ የለም፣ ነገ እነግርሃለሁ ደስ የሚል ነገር ነው" አለችው።

"ምነው ውቢትና ክብሩ ታረቁ እንዴ" አላት ዐይኑ በትንሹም ቢሆን ብርሃን እየፈነጠቀ።

"ከሱም የተሻለ! እነግርሃለው በሰፊው" ብላው ሄደች።

Scanned by CamScanner



ክብሩ የደስታን ጉዳይ እያሰላሰለ ነበር ወደ እስር ቤቱ ሃኪም ቤት ያቀናው። ሰብለ ደውላ የደስታን ሁኔታ ስትነግረው በአጭር ጊዜ ውስጥ የደስታ በጠና መታመም በጣም ነበር ያስደነገጠው። የመጨረሻ ንግግራቸው አሁንም በጆሮው እያቃጨለበት ነው። የደስታ ከጊዜ ወደጊዜ ነጭናጫ መሆን እያሳሰበው ቢመጣም ነገሩ እንዲህ ይከፋል ብሎ አልገመተም። ለምን? አለና ራሱን ጠየቀ።

" የመኖር እርግጠኝነት " አለ መልሶ፣ ደስታ እንዲህ ብሎ እንደሚመልስለት በማሰብ። ክብሩ ደስታን ሊጠይቀው የሄደ ቀን በውቢት ጉዳይ ቢጋጩም ተመልሶ እንደሚያገኘውና በጉዳዩ እንደሚነጋገሩበት ሙሉ በሙሉ ርግጠኛ ነበር። አሁን ግን የሚገናኙት ደስታ በጠና ታሞ ይህን አይደለም ተራ ወሬ እንኳን ማውራት በማይችሉበት ሁኔታ ነው። ነገርን በጊዜው አለመቋጨት እንዴት ይቆጫል? የሚወዱትን ጓደኛስ በፍቅር ደህና ሁን እስከምንገናኝ አለማለትስ? መኖር መታለል ነው፣የሚቀር አይመስልም።

ክብሩም በመኖር ተታሎ ከጓደኛው ጋር በግጭት መለያየቱ አንገበገበው። ወደ ሆስፒታሉ ሲደርስ መኮንን ቀድሞት ደርሷል። ከመኮንን ጋር የውቢት ጓደኛ አይዳን ሲያይ ተገረመ። ድብቁ የአይዳ ጓደኛ መኮንን ይሆናል ብሎ አስቦ አያውቅም ነበር። ጓደኞቿም ቢሆኑ መኮንን የአይዳ ፍቅረኛ መሆኑን የሚያውቁ አልመሰለውም።

Scanned by CamScanner

መኮንን ፊቱ በጣም ተረባብሿል። አይዳ ለክብሩ ፊት አልሰጠችውም። የውቢት ጓደኞች በጠቅላላ በአድማ እንደዘጉት ስለሚያውቅ ብዙም አላሳሰበውም።

ደስታ ከአልጋው ላይ እንደተንጋለለ ሦስቱንም እየተቁለጨለጨ ያያቸዋል። ድንገት

"ሄይ ቁልል መጣህ? እንሂዳ" አለ ደስታ

ክብሩ ትንሽ ግራ በመጋባት "የት ነው የምንሄደው? ደህና ነህ?" አለ።

"ሰርጉ ጋር ነዋ" አለ ደስታ።

ክብሩ አናቱን አንዳች ነገር ለሁለት የሰነጠቀው ያህል ደነገጠ። ከድንጋጤው ብዛት ሳያስበው እጁን ወደ ግራ ደረቱ በመስደድ ልቡ ፈርጥጣ አለመውጣቷን አረጋገጠ።

ደስታ እየቃዥ ነበር። ክብሩ ደግሞ እንደ ሃኪምነቱ በሽታው ምንም ይሁን ምንም አንድ ሰው መቃዥት ከጀመረ ህመሙ የከበደ መሆኑን ማሳያ መሆኑን ጠንቅቆ ያውቃል። የቀኝ እጁን እንደምንም በማላቀቅ የደስታን ግንባር እንደመንካት ብሎ ትኩሳት ይኖረው እንደሆን ለማጣራት ሞከረ።

የደስታ ግንባር ምንም አይነት የሙቀት ስሜት አልነበረውም። የባሰውን ደነገጠ። ቅዥቱ ትኩሳት ከሚያመጣ ህመም ጋር የተያያዘ ካልሆነ በጭንቅላቱ ውስጥ አንዳች ነገር ኖሮ ነው ማለት ነው ሲል አሰበ። በዚህ ቅፅበት ነገሩ ሁሉ ተገጣጠመለት። መኮንንና አይዳን ከአልጋው ጠርዝ ትታቸው ሃኪሙ ወዴት እንደሚገኝ በመጠየቅ ሮጥ ሮጥ እያለ ሄደ። መኮንን ና አይዳ ተከተሉት፤ ደስታ ሦስቱም ሲሯሯጡ በፈገግታ ያያቸው ነበር።

ክብሩ ሃኪሙን እንዳገኘው ማን እንደሆነ ካስተዋወቀ በኋላ፤ "ዶ/ር ደስታ ወደ ሌላ ሃኪም ቤት መሄድ አለበት" አለው። ሃኪሙ ትንሽ እንደማሰብ ብሎ፤

Scanned by CamScanner

"ታራሚ ደስታ ዶ/ር ነው እንዴ" ሲል ክብሩን ያልተጠበቀ ጥያቄ ጠየቀው።

"አዎ። አላወቅክም ነበር?" አለ ክብሩ ለጊዜው እሱም ቁም ነገሩ ተረስቶት

"እረ ወደ መጣንበት" ብሎ ዳኛው መኮንን ሁለቱንም ሃኪሞች አነቃቸው።

"አዎ" አለ የእስር ቤቱ ሃኪም "ለምንድነው የሚሄደው" ሲል ክብሩን ጠየቀው።

ክብሩ የገመተውን አስረዳው "ይኸውልህ ከወራት በፊት ደስታ የመኪና አደጋ ደርሶበት ለጥቂት ደቂቃዎች ራሱን ስቶ ነበር" ብሎ ሲጀምር

"እሺ" አለ ሃኪሙ። መኮንንና አይዳ የሚባለውን በጥሞና እየተከታተሉ ነው።

"ከዚያ ለጊዜው ደህና ነበር እየቆየ ግን ትንሽ ራስ ምታት ምናምን ጀመረው፤ በኋላም ደግሞ ባልተለመደ ሁኔታ መነጫነጭ ጀምሮ ነበር አሁን እንደዚህ ሆነ" ብሎ ንግግሩን ጨረሰ። የእስር ቤቱ ሃኪም "ገባኝ ገባኝ አዎ ልክ ነው መሄድ አለበት" አለ ተመልሶ ወደ ህክምና ክፍሉ እየገባ። መኮንንና አይዳ በሁኔታው ግራ ተጋቡ። ክብሩ የተናገረውን ሲጨርስ ከሃኪሙ ጋር ቢግባባም ለእነሱ ምንም አልገባቸውም።

የእስር ቤቱ ሃኪም ተገዢውን የወረቀት ስራ ሲሰራ መኮንን ወደ ክብሩ ጠጋ ብሎ "ምንድነው የሆነው" አለው።

"ከወራት በፊት አደጋው ሲደርስ" ብሎ ሲጀምር

"እሱንማ ስማን እኮ አሁን ምንድነው የሆነው" አለ መኮንን ኮስተር በማለት ምናልባት ክብሩ በሚገባው ቋንቋ ቢያስረዳኝ ብሎ በመመኘት። ክብሩ ትንፋሹን በመሳብ ራሱን ካረጋጋ በኋላ

Scanned by CamScanner

"ምናልባት በአደጋው ጊዜ በጭንቅላቱ ውስጥ ደም ፈስሶ ይሆናል" አለ።

"ስለዚህ" አለ መኮንን።

"ከጊዜ ብዛት ያ የፈሰሰው ደም አንጎሉን እየተጫነው መጥቶ ሊሆን ይችላል፤ አሁን የምናየው ክስተት የተፈጠረው" ሲል አብራራ። ክብሩ።

"ታዲያ ይህ ሲሆን አንዳችሁም ይህ ይመጣል ብላችሁ አላሰባችሁም?" አለ መኮንን በመገረም፤ ነገሩ ትንሽ የማወቅ ችግር እንደሆነ ስላልተረዳ

"በጊዜው ደም መፍሰሱን ብናውቅም መጠኑ አነስተኛ ስለነበር በራሱ ጊዜ ይጠፋል ብለን አስበን ነበር" አለ ክብሩ የመከላከያ ሃሳብ ለማቅረብ ያህል።

"እና አሁን ምንድነው የሚደረገው" አለ መኮንን ወደ መፍትሄው መሄድ እንደሚበጅ በማሰብ።

"በአስቸኳይ ወደኛ ሆስፒታል ሄዶ ችግሩ ይኼ ከሆነ ቀዶ ህክምና በማድረግ በጭንቅላቱ ውስጥ የረጋው ደም መውጣት አለበት" አለ ክብሩ።

አሁን መኮንን በተራው አናቱ ተሰነጠቀ። ትንሽ እንደመንገዳገድ ስላደረገው ከጎኑ ሆና በድን የመሰለችውን አይዳን ተደገፋት።

Scanned by CamScanner



ሰብለ ከቤቷ ስትወጣ ጥሩ ስሜት እየተሰማት ነበር። ደስ ብሏታል። ብዙ ነገሮች ተሳክተውላታል። ክብሩና መኮንን ደስታን አይተው ወደነ ደስታ ሆስፒታል ሊያዛውሩት እንደሆነ አውቃለች። ከዚያ በተጨማሪ ለደስታ የምታበስረው ትልቅ የምስራች አላት። በሆዷ ህይወት እየበቀለ ነው። ልጅ፤ ሌላ ሰው እያበቀለች ነው። ይህ ሰው ደግሞ የደስታም ነገሮች ይሆኑለታል ዛሬ። በዚህም ሰብለ ተደስታለች።

ከእስር ቤቱ ሆስፒታል ስትደርስ መኮንንና አይዳ ጎን ለጎን ተኮራምተው እንደተቀመጡ አየች። አይዳ ለምን መጣች ብላ ራሷን ጠየቀች። እንዴ አይዳ እንዴት መጣች አለች አሁንም ለራሷ ድንገት ውይ የተደበቀው የአይዳ ፍቅረኛ መኮንን ባልሆነ ብቻ ብላ እያሰበች አጠገባቸው ስትደርስ የሁለቱም ፊት ያኮፈኮፈ ግድግዳ መስሎ ተጨራምቷል

"ምነው ደህና አይደላችሁም?" አለች።

"ደህና ነን ሰብሊ" አለ መኮንን። ክብሩ ከጎን ከሚገኘው ክፍል ወረቀት ይዞ ሲወጣ ተገጣጠሙ

"ምነው ችግር አለ?" አለችው እሱንም። ክብሩ ምን እንደሚመልስላት በማሰብ ላይ እያለ የእስር ቤቱ ሃኪም ከኋላው ብቅ ብሎ "አምቡላንሱ ተዘጋጅቷል" አለ። ሰብለ ትንፋሿ መለስ አለላት።

Scanned by CamScanner

"ደስትሽ ሊሄድ ነው? ጎሽ አሁን ደስ ይለዋል" አለች። ሦስቱም ምንም መልስ አልሰጧትም። እሷም ነገሩን ችላ በማለት ክብሩን ተከትላ ወደ ደስታ መኝታ አቀናች።

ደስታ ፊቱ ፈገግ እንዳለ ተቀበላቸው።

"ደስትሽ እንዴት ነህ?" አለችው።

"በጣም ደህና ነኝ" አላት።

"ጎሽ በቃ አሁን ልትሄድ ነው እሺ" አለችው።

"አይ በጣም ዘገየሁ" አላት ሲመልስ በረጋ ፈገግታ ቢሆንም የለመደችውን የደስታን መቀት ከንግግሩ አላገኘችም።

"በቃ አሁን መሄድ አለብኝ በጣም ቸኩያለሁ" አለ ደስታ።

"እሪ አትቸኩል" አለች ሰብለ ደስታን ለማረጋጋት በመጣር።

"ብዙ በሽተኞች እየጠበቁኝ ነው" አላት።

"ምን?" አለችው ግራ ግብቷት።

"በቃ እንደውም ልተኛ" ብሎ ዐይኑን ጨፈነ።

ሰብለ ግራ ገብቷት ሦስቱንም አየቻቸው፣ የሆነውን ቢያብራሩላት ብላ። ክብሩ ትክሻዋን ሳብ ለማድረግ ሲሞክር አትንካኝ በሚል መነጨቀችው። እሷም የውቢት ተደራቢ እንደሆነች ያውቃል። ምላሿን ቸል በማለት የሆነውን አስረዳት። ሰብለ ክብሩ የደስታን ሁኔታ እያስረዳት አካባቢዋ ያሉ ነገሮች ሁሉ ከዐይኖቿ እየራቁ አነሱባት፣ ብቻዋን የቀረችና ጭውውው..... የሚል ድምፅ ብቻ የምትሰማ መሰላት። "መኖር የማትነቂበት ህልም ነው" ያለው የደስታ ድምፅ ታወሳት።

Scanned by CamScanner

ደስታን የተወሰኑ ባለሙያዎች መጥተው በአልጋ እየገፉ ወደ አምቡላንሱ ወሰዱት። ሰብለ በደመነፍስ እየተጎተተች ተከተለቻቸው። ሌሎቹም እንዲሁ። ደስታ ፈገግ እንዳለ ነው።

"እያምርም?" አላት ወደ ሰብለ እየተመለከተ።

"ምኑ?" አለች የሞት ሞቷን።

"ሙዚቃው" አላት አሁንም በፈገግታ ።

ሰብለና ክብሩ በአንቡላንስ ተጭነው፤ ደስታ የባጥ የቆጡን እያቃዥ፤ ደስታ ከተማረበት፣ ከሰራበትና፣ከሚሰራበት ሆስፒታል የመጨረሻው ሰው ሆኖ ተመለሰ። ደስታ በዚህ ሆስፒታል ውስጥ ተማሪም፣ አስተማሪም፣ ሃኪምም ሆኖ ኖሮ አሁን ታማሚ ሆኖ ገባ።

Scanned by CamScanner

አርባ አንድ

ክብሩ በመጠኑም ቢሆን ቀለል ብሎታል። ቢያንስ ይኼ ፊላጭ ቆራጭ የሆነበት ቦታ ነው። እንደምንም ብሎ ደስታን እንደሚያተርፈው ያምናል። ነገሮች ግን እንደሚያስበው አልቀለሉም። በሆስፒታሉ ውስጥ ምንም አልጋ ስላልነበረ ደስታ በድንገተኛ ክፍል የበሽተኛ ማመላለሻ አልጋ ላይ እንዲጋደም ሆነ። ክብሩ ይህም ይሁን ብሎ በቀጥታ ቀዶ ህክምና ሊሰራለት ወደሚችል ሃኪም ደወለ። ሃኪሙ ሩቅ ቦታ እንደሚገኝና በተቻለው ፍጥነት እንደሚመጣ ነገረው።

ሰብለ መዘግየቱ ምንም አልጣማትም። ከነሱ ቀድማ እዚያው ሆስፒታል ለጠበቀቻቸው ውቢት "ለምን የግል ሆስፒታል አንወስደውም" አለቻት።

ውቢት "እስረኛ ስለሆነ በግል ሊታከም አይችልም" አለች ቀላል መልስ በመስጠት "በዚያ ላይ የሚያስፈልገው ህክምና እንደሆነ በቀላሉ በግል ቦታ አይገኝም" ብላ ጨመረችላት።

"እና ዝም ተብሎ ነው የሚታየው?" አለች ሰብለ።

"ይመጣል ሃኪሙ። እስከዚያ እኮ ሌሎች እየመረመሩት ነው" አለች ውቢት ሰብለን ለማፅናናት።

"የዘገየ መፍትሄ፤ ምን መፍትሄ ይሆናል" አለች ሰብለ ውቢት መልስ አልነበራትም። ክብሩ በተቀመጠበት አግዳሚ ላይ ሆኖ ሁሉን ማድረግ ይችል ይመስለው በነበረ ቦታ ምንም ማድረግ አለመቻሉ ገረመው።

Scanned by CamScanner

አፍጣ ሁለት

ደስታ ድንገተኛ ክፍል ውስጥ ከተኛ ሦስት ቀናት አለፉት። ሰብለ ሦስቱንም ቀን በድንገተኛው ወለል ላይ ተኝታ ትጠብቀዋለች።ሃኪሞቹ ደስታን በአግባቡ ከመረመሩ በኋላ ክብሩ እንደጠረጠረው በአንጎሉ ውስጥ ደም መፍሰሱን አረጋግጠዋል። ቀዶ ህክምና እንደሚያስፈልገውም ወስነዋል። በቀዶ ህክምና ክፍሉም ለቀዶ ህክምናው የሚያስፈልገው መሣሪያ በሙሉ ተዘጋጅቷል። ሆኖም ግን ለሦስት ቀናት ቀዶ ህክምናውን ማድረግ አልቻሉም።

ቀዶ ህክምናውን ማድረግ ያልቻሉበት ምክንያት ከቀዶ ህክምናው በኋላ ደስታ የግድ ጊዜያዊ የመተንፈሻ ማሽን ላይ መቀመጥ ይጠበቅበታል። ያንን ማድረግ ካልቻለ ከቀዶ ህክምናው በኋላ ደስታን በህይወት ማቆየት አዳጋች ይሆናል። በሆስፒታሉ ውስጥ ያሉት የጊዜያዊ መተንፈሻ ማሽኖች ሦስት ብቻ ናቸው። ሦስቱም ደግሞ በሌሎች ህመምተኞች ቀድመው ስለተያዙ አንዱ ህመምተኛ እስኪድን ወይንም እስኪሞት ድረስ ደስታ በድንገተኛ ክፍል ተኝቶ መጠበቅ ግድ ሆኖበታል። ደስታ የመተኛ አልጋም፣ የመተንፈሻ ማሽንም ማግኘት አልቻለም። እዚህ ሆስፒታል ከመጣ በኋላ ቅዠቱ እየለቀቀው ሄደ ጠበቅ ያለ እንቅልፍ በሚመስል ሰመመን ተተክቷል። ሃኪሞቹ አንዳንድ ጊዜ ደረቱን እየተጫኑት ሌላ ጊዜም አልኮል ወደ አፍንጫው በማስጠጋት ሊያነቁት ይሞክራሉ።

አራተኛው ቀን ላይ ደስታ ሙሉ በሙሉ ራሱን ሳተ። በምንም መልክ ሊነቃ አልቻለም። ቅዠትም፣ የሰመመን እንቅልፍም የለውም። ጥልቅ

Scanned by CamScanner

እንቅልፍ መሳይ ሁኔታ ውስጥ ገብቷል። በዚሁ ቀን አንድ መኝታ አልጋ ስለተገኘ ደስታ ከድንገተኛ ክፍል ወደ መኝታ ክፍል ተዛወረ። ሰብለም አብራ ተዛወረች።

ደስታን ሁሉም ሰው ረዳው፣ አዘነለት፣ ጠየቀው፣ አሰበለት፣ ተጨነቀለት፣ ፀለየለት ቢሆንም ግን እነዚያ ሦስት ማሽኖች አሁንም አልተለቀቁም። እነዚያም ሰዎች ብዙ አሳቢና ፀሎተኛ ሳይኖራቸው አልቀረም። ህመም፣ መቸገር፣ መከራ እና ሞት የሰው ሁሉ እኩልነት መገለጫዎች ናቸው።

ደስታ መኝታ ክፍል ከገባ አራት ቀናትን ያህል ቆይቶ ትንፋሹ መለወጥ ጀመረ። በአፍንጫው አየር አብዝቶ ይስብና በጣም በጉልበት መልሶ ያወጣዋል። ሃኪሞቹ ተጨነቁ፤ እየሆነ ያለው ገብቷቸዋል። መፍትሄውንም ያውቃሉ። ከአንዱ ማሽን ነቅሎ ወደሌላው ማድረግ በህግ የተከለከለ ነው። ማሽን ላይ ያለው ታማሚ የሚሞት መሆኑ ቢታወቅም እንኳን ማሽኑን መንቀል ክልክል ነው። በዚህ ምክንያት አንድ ሰው አንድ ማሽንን ለወራት ይዞ ሊተኛበት ይችላል እስከሚሞት ድረስ። በዚህ መካከል መትረፍ የሚችል ማሽን ፈላጊ ቢሞትም ከማዘን ውጪ ምንም ማድረግ አይቻልም።

የደስታ አተነፋፈስ እየጠነከረ በመሄዱ ሃኪሞቹ ሃሳብ ገብቷቸዋል። የደረቱ የመተንፈሻ ጡንቻዎች ተዳክመው ጭርሱን መተንፈስ እንዳያቅተው ሰግተዋል።

ደስታ አልጋ ይዞ ከተኛ በስድስተኛ ቀኑ አንድ መልካም ነገር ተከሰተ። ከሦስቱ ማሽኖች አንዱ ላይ ሦስት ወር ከአስራ ሠባት ቀን የተኛ ሀምሳተኛ ሞተ። ይህ ለደስታ ወገኖች ደስታ ነበር። አንዱ ሲሞት ለሌላው ህይወት መሆኑ እውነት ሳይሆን አይቀርም።

ደስታ በቀጥታ ወደ ፅኑ ህመማን መታከሚያ ክፍል ተዛውሮ የመተንፈሻ ማሽኑ ተገጠመለት። ሰብለም ከጽኑ ህመማን መታከሚያ ክፍል ትይዩ ወደሚገኘው ኮሪዶር ተዛወረች፤ የመተኛ ካርቶኗን ይዛ።

Scanned by CamScanner

ደስታ የመተንፈሻ ማሽን ቢያገኝም ቀዶ ህክምና የሚቋቋምበት አቅም ስላልነበረው ቀዶ ህክምናውን ማድረግ ግን አልተቻለም። በመተንፈሻ መሣሪያው ላይ እያለ ሃኪሞቹ ሌላ ችግር መከሰቱን አረጋገጡ።

Scanned by CamScanner

አፍቅሮ ሞቱ

ሃኪሞቹ የደስታ አንጎል መስራት ማቆሙን አረጋግጠዋል። ደስታ እንደዋዛ በማሽን ላይ መኖር ከጀመረ ሳምንታት አልፈዋል። ጠያቂዎቹም ቀንሰዋል። ሰብለም እቤቷ ማደር ጀምራለች። ክብሩና ውቢት ሰዓታቸው እንዳይገጣጠም ተጠንቅቀው በየሰዓቱ ያዩታል። ከማየት በስተቀረ ግን አንድም የሚረዱት ነገር አልነበረም።

ክብሩ ሌላ ስራ በማይሰራበት ጊዜ ሁሉ ስለ ደስታ ያስባል። ደስታ እንዴት በማሽን ላይ ይኖራል ብሎ ራሱን ደጋግሞ ይጠይቃል። በማሽን ላይ መኖር እውን መኖር ነው? ከአለመኖር ጋር ትንቅንቅ እንጂ የሚለው የደስታ መከራከሪያ ሁልጊዜ ይታወሰዋል።

በሆስፒታላቸው ውስጥ የማሽን እጥረትና ከዚህ ጋር የተያያዙ ችግሮች በተነሱ ቁጥር ደስታ ሰዎች የሚሞቱ መሆናቸው ከተረጋገጠ ያለ አግባብ ህይወታቸውን በማራዘም የነሱንም ስቃይ ማብዛት፤ ሊተርፍ የሚችል ሰውንም ዕደሜ ማሳጠር የለብንም ብሎ ብቻውን ይከራከር እንደነበር ክብሩ ያስባል።

"ሰው ከተወለደ ጀምሮ እስከሚሞት ድረስ ካለመኖር ፍርሃት ጋር ለምን ይተናነቃል" ይል ነበር።

አሁን በእሱ በራሱ ደረሰ አለ ክብሩ ። ግን በእሱ በራሱ ፍቃድ የሆነ አይደለም ሲል አሰበ። ውቢት አብራው ብትሆንና ይህን ቢያወራት ተመኘ፤ ነገሩ ሁሉ በአጭር ጊዜ መደበላለቁ አሳዘነው። ደስታን

Scanned by CamScanner

አጥቷል። ደስታ በሆነ ተዓምር ቢተርፍ እንኳን በአንጎሉ ላይ በደረሰው ጉዳት ምክንያት አካሉ እንጂ 'ሰው፡ እነቱ' እንደማይመለስ አውቋል።

"አሁን እኮ ደስታ የለም" አለ። ብቻውን በማውራቱ በመቀጠል "በፊትም አልነበረም። ወደፊትም አይኖርም።" የደስታ መፈክር ታወሰው። ደስታ ከሞት በኋላ ህይወት የለም ብሎ ነበር እንዴ የሚያምነው ብሎ ራሱን ጠየቀና የደስታን ምላሽ አስታወሰ።

"ከሞት በፊትና ከሞት በኋላ ህይወት የለም ብሎ መጠየቅ ይገርመኛል። ከሞት በፊትና ከሞት በኋላ ያለው ህይወት አንድ ሊሆን እንዴት ይችላል? አንድ አይደለም። ከሞት በፊት እኮ መኖር አለ፤ ከሞት በኋላ አለመኖር። ሁለቱ እንዴት አንድ ሊሆኑ ይችላሉ? መኖር እኮ መታደል ነው። መመረጥ ነው። ብዙዎቻችን ሳንኖር ነው የምንሞተው። እንዳንሞት ስንጠነቀቅ። ከሞት በኋላ ህይወት ይኖር ይሆናል ። መኖር ግን የለም። እንዲህ በምናውቀው መንገድ መኖር የለም። አንድ ጊዜ ብቻ የሚመጣውን መኖር ባናባክነው ምነኛ ደስ ይል ነበር"

ክብሩ የራሱ መኖር ግራ ገባው። ደስታ ከውጭ ያለ ተቆጣጣሪው ነበር። ከተቀመጠበት ተነስቶ በቀጥታ ደስታ ወደተኛበት ክፍል አመራ። በክፍሉ ውስጥ የሦስቱ ማሽኖች ኩርፍታ ጮክ ብሎ ይሰማል።

ክብሩ ከደስታ አልጋ ጋር ጠጋ ብሎ ለመቀመጥ ሞከረ። ፍርሃት ተሰማው። ደስታን በአግባቡ እንኳን አቅፎ ስሞት እንደማያውቅ አሰበ። በጣም ናፈቀው። እንዴት አድርጎ ይመልሰው? ደስታ ለህይወቱ ምን ያህል እንደዋለለት አሰበ። መዓዛ ፣የማያውቀው ልጅ፣ ውቢት፣ ሰብለ፣ ስራ፣ ጨዋታ፣ቁም ነገር ሁሉም ነገሩ ውስጥ ደስታ ነበር። በመኖሩም ህይወቱን ምሉዕ እንዳደረገለት አሰበ።

የደስታም ህይወት የጎደለ አልነበረም። እንደውም ከእሱ በላይ የኖረ አለመኖርን ያልፈራ ሆኖ ታየው። አንሶላውን ለማስተካከል ሊገልጥ የደስታ ቆዳ ከመቀመጫው አካባቢ ተላልጦ አየ። ደስታ በስተመጨረሻ

Scanned by CamScanner

በወጉ የሚያገላብጠው ሰው እንዴት ሊጠፋ እንደቻለ አሰበ። ጓደኛው መቆሳሰሉ አሳዘነው።

"ይሄ መኖር እንዳልሆነ አንተም እኔም እናውቃለን። እኔ በአንተ ቦታ ብሆን አንተ ቀድመህ ታደርግልኝ የነበረውን ላድርግ። አንተ ብትሆን እስክቆስል አትተወኝም ነበር። እስክሸትም አትታገስም። አንተ መኖርን ታውቃለህ ወዳጄ። እኔ አሁን ወደምትናፍቀው፣ ወደምትሰብክለት አለመኖር ልሸኝህ።

ሰው አለመኖሩ ላይቀር መኖሩን ለምን ያመሰቃቅላል ትል ነበር። መልሱን አሁንም አላውቅም፤ አንተም መጠየቅህን እንጂ ለመልሱ ቁብ አልነበረህም። ደህና ሁን ወዳጄ" ብሎ ከደስታ አፍንጫና አፍ ላይ የተሰካውን ማሽን መንቀል ጀመረ። የሚያደርገው ጥፋት ቢሆንም ፤በጣም በጥንቃቄ እና በእርጋታ ነበር።

መሣሪያው እንደተነቀለ ደስታ ያጣጥር ጀመር። በጣሩ መካከል ድንገት ዐይኑን ገለጠ። ክብሩ ደስታ አተኩሮ ያየው መሰለው። በሰከንዶች ውስጥ ደስታ አሸለበ፤ ሞተ። አረፈ። ወደ አለመኖሩ ተሸኘ። ክብሩ የማይፈስ እንባ አይኑን ሲወጋው ተሰማው። ትክክል ማድረጉን ለአፍታም አልተጠራጠረም።

የደስታን ማረፍ የልብ ምት መቆጣጠሪያ መሣሪያው ሲያሰማ ተራኛ የነበሩት ነርሶች ከነበሩበት ተሯሩጠው መጡ።

ክብሩ ሁለት እጆቹን ወደፊት አጣምሮ ለእስር በማዘጋጀት "እኔ ነኝ የነቀልኩት" ብሎ ነፍስ ማጥፋቱን አመነ። በዙሪያው የነበሩት ሁሉ መጮህ ጀመሩ። ክብሩ ሁሉንም አስተውሎ አያቸው። ደስታ እንደሚሞት የማያውቁ ይመስሉ ነበር።

በጩኸቱና በግርግሩ መካከል አንደኛው የጥበቃ ሰራተኛ ወደ ክብሩ በመጠጋት ከጀርባው ጨመደደው። ሌላኛው "አረመኔ" ብሎ በጥፊ አጮለው። ለሰከንድ ያህል ጨለመበት። ከዚያ በተከታታይ የዱላ መዓት ይወርድበት ጀመር።

"ደስታን ያውቁት ነበር?" ሲል አሰበ።

Scanned by CamScanner



“አልሰማሁም አላየሁም

አልነበርኩም እኔ አልኖርኩም

አትልም!”

ደስታ፤ ተወዳጅ ጓደኛ፣ ወንድም፣ ፍቅረኛ እና ታሳቢ አባት

“ከዚህ በላይ እንዲፃፍለት የሚፈልግ አይመስለኝም” አለች ሰብለ ከደስታ መቃብር ድንጋይ ላይ የተፃፈውን ከውቢት ጋር እየጎበኙ ነበር።

“ሊከራከር ይችላል” አለች ውቢት በፈገግታ። በእርግጥም ሊከራከር እንደሚችል እያሰበች።

“አንቺ የታደልሽ ነሽ” አለች ሰብለ “ቀድመሽ ስላወቅሽው ብዙ ትዝታ አለሽ” ብላ እንደመተከዝ አለች።

“አንቺ ደግሞ ምትኩ አለሽ” መለሰች ውቢት።

“እሱስ አይተካም። ግን ማስታወሻ አለው” አለች ሰብለ።

“ደስታ፣ ሰው ቢያንስ በሦስት ነገር አለመኖርን ለማሸነፍ ይጥራል። ይል ነበር” አለች ውቢት በትዝታ እየሄደች።

Scanned by CamScanner

"ብልጅ" አለች ሰብለ ሆዷን እየዳበሰች።

"በመልካም ወይም በክፉ ስራ" ቀጠለች ውቢት።

"ከሞት በኋላ ህይወት" አለች ሰብለ አይኗን በመቃብሩ ላይ እንደተከለች።

"ማን አይቶ በነገረን" መለሰች ውቢት።

ለአስተያየትም

dawit.wondimagegn@gmail.com

Scanned by CamScanner



ዶ/ር ጳዉት ወንድማገኝ
በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

አእምሮ ህክምና ከፍል ተባባሪ ፕሮፌሰርና የትምህርት ክፋሉ ሀላፊ ነዉ። በተጨማሪም በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል በአእምሮ ህክምና ክፍል ያገለግላል።

ፍልስፍና በህክምና፣ በአእምሮ ህክምናና በህክምና ስነ-ምግባር አስተምህሮ ላይ ሊኖረው በሚገባው ፋይዳ ላይ ያተኮረ የምርምር ዝንባሌ አሳዉ።

የቀደመዉ ባህል፣ፖለቲካ፣ ታሪክ፣ ማህበራዊ ኑሮና የኢኮኖሚ ጥምረት በአሁንና በወደፊት የጤና አገልግሎት ሰርአት ላይ ያሳቸውን የወል ሚና ያመረምራል።

ከዚህ ቀደም "ቤት የሙቱ ሀሳቦች" የሚል የግጥም መድብል አበርክቱዋል።

Scanned by CamScanner

መጠየቅ የሚፈቀድና የሚገባ መሆኑን ብቻ ሳይሆን በመጠየቅ ዓለማችንን መፍጠር
እንደምንችል ያሳየኝ መጽሐፍ ነው።

ወ/ሮ ሶሎሚ ታደሰ

ይህ ድርሰት ጣሙራ ተቃራኒ ሃታ ባህርያትን ፈጥሮ በገሃዱ ዓለም የምናውቃቸው እስኪመስሉን
ድረስ ገጠመኞቻቸውን ያስዳስሰናል። ከሐኪም ቤት፣ምግብ ቤት ፣ማረሚያ ቤት፣ መኖርያ ቤት፣
መቃብርቤት እያሰ ከህይወት እስከ ሞት ሁለመ ጽንፍ ያለውን ሂደት ያሥቃኘናል። በዘርካታ
ገጥሞችና በግጥም መድበሉ የምናውቀው ገጣሚ ሐኪምነቱ ፀምህርነቱና በጓሳ የደረበው
የፍልስፍና ሰውቀቱ ከሰብዓዊነቱ ጋር ተዳምረዙ ደራሲ ዳዊት ወንድማገኝ መፈጠር መመለድና
መኖርን ባንድ መገን በሲላ ገጽ ደግሞ የአለመኖርን ፍልስፍና በመበርበር ያስደምመናል።
በዚህ ድርሰት ውስጥ መተሳሰብ፣ ፍቅር፣ጥላቻ፣ቅናት፣የጊዜ አጠቃቀም ሥርዓት፣ ሥልጣን፣
ይሉኝታ፣ ጉራ፣ መኖር፣ መሞት የመሳሰሉት ከመኖር እስከ አለመኖር ባለው ቂት ውስጥ ያሳቸውን
መስተጋብር በሚገባን ቋንቋ ስላቀረበልን በአዲሱ ካባው ዳዊትን "ዕድግ ተመንደግ እያልኩ
ለተደራስያኑ መልካም የንባብ ጊዜ እመኛለሁ!"

ዶ/ር መስፍን አርአያ
የአእምሮ ሐኪምና መምህር

"አለመኖር"
በአንድ መፅሐፍ ውስጥ ሃሣብን በዚህ መልኩ ማንሳት ይቻላል እንዴ? መፅሐፉን ሳነበው
መጀመርያ ወደ አሰምሮዬ የመጣ ጥያቄ ነው። በመፅሐፉ ውስጥ ያልተነሳ ሃሳብ የለም ማለት
ይቻላል፣እኔን የመሰጠኝ ግን የሃሳቦቹ በግርድፉ መነሳት ሳይሆን ሃሳቦቹ የታዩበት አሙታርና
ጥልቀት ነው። ልማዳዊ ከሆነው ሰይታ ውጪ ነገርችን ማየትም ሆነ መመርመር ውጉዝ በሆነበት
በዚህ ማህበረሰብ፣"አለመኖር" ነገርችን ከመሰረታቸው በመነትነቅ "ለካ እንዲህም አለ!"
ወደሚል መደመም መክተት ብቻ ሳይሆን የሰይታ መነሰራችንን እንደ አዲስ ወደ መምረጥና
ማስተካከል ትገፋለች ቁምነገሩም እሱ ይመስለኛል።

ዳንኤል ለማ

በማንበብ የማያስችግር ትረካ የታሪኩ አስተዳደግ ፈጣን በአስተማሪነቱ እንደ ግለሰብ
ማሕበረሰብ አገርና መንግስት ሁልጊዜ ከአፍ ዉጭ ያለውን ማየት መገምገምና አመቅልሃለሁ
ማለት ብቻ ሳይሆን ራስን ወደ ሠዓዊ መመልከት በጣም አስፈላጊ መሆኑን የሚያሳይ ከፍተኛ
መልእክትን ያዘለ የፍልስፍና ሥራ ነዉ ማጋነን እንደማይሆን አንባቢውም አንብቦ
እንደሚያረጋግጥ አልጠራጠርም ::

ዶ/ር አብነት ታፈሰ
የሠስተ ደዊ እና የነርቭ በሽታዎች ሐኪምና መምህር

ISBN 978-99944-942-6-2

አንድ መቶ ሃያ ብር
10 USD

Falcon Printing +251 11 551 7114
+251 941 333 333

Scanned by CamScanner